## ኤዲቶሪያል ፖሊሲ

ኢቢሲ ኤዲቶሪያል ፖሊሲ ኮርፖሬሽኑ ለሚከተለው ሙያዊ ስነ-ምግባር እና ለሚሰጠው የአገልግሎት ጥራትና ደረጃ መጠበቅ ዋነኛ መሠረትና መነሻ ነው፡፡ በዚህ ኤዲቶሪያል ፖሊሲ የሚካተቱ ይዘቶች በጥቅሉ ኮርፖሬሽኑ ስለሚገዛባቸው ሀገር አቀፍ ሕጐችና ብሮድካስት ነክ ድንጋጌዎች ሁልጊዜ ታሳቢ በማደረግ ወሳኝ የህዝብ ጥቅሞችና ለኮርፖሬሽኑ የብሮድካስቲንግ ውጤቶች የዕለት ተዕለት የሥራ መመሪያ ይሆናል፡፡




## የይዘት ዘርፍ ማኑዋሎች ጥራዝ

በየደረጃው የተዋቀሩትን ክፍሎች ዝርዝር አሰራርና አደረጃጀት እንዲሁም የተጣለባቸው ግዴታና ኃላፊነት ያብራራል፡፡ እንዲሁም ለውስጥና ለውጭ ፈጻሚዎችና ተጠቃሚዎች ግልፅነት ይፈጥራሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ ከመስከረም 2007 ዓ.ም ጀምሮም ሥራ ላይ የዋሉ ናቸው፡፡

ኢቢሲ በአሰራሩ ፍትሐዊነት፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት የሚያሰፍኑ ሌሎች ተጨማሪ ማኑዋሎችም በማዘጋጀት ተግባራዊ ያደረጋል፡፡ይህም በኤዲቶሪያል ፖሊሲው ላይ የተቀመጠውን በመርህና በአሰራር የመመራት መርህ እውን ለማድረግ ነው፡፡

**<u>በይዘት ዘርፍ የዜና አሰራር መመሪያ</u>**

የአሰራር መመሪያው የዜናን መሠረተ ሐሳብ ፣ይዘት፣ ባህሪና መርሆዎችን ከመያዝ ባሻገር አንድ የዕለት ዜና ዘገባ ከመነሻ ሐሳብ (story idea) አንስቶ እስከ ስርጭት ፍጻሜው ድረስ በየደረጃው የሚያልፍበትን ሂደት ፣ የሚጠይቃቸውን ግብአቶችና ተሳትፎዎች አካትቶ የያዘ ነው፡፡ ሰነዱ በዋናነት የዜና ክፍል አሰራርን፣ በዜና ሽፋን የሚያገኙ ፖለቲካዊ፣ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሌሎች ጉዳዮችን ይዟል፡፡ እንዲሁም የዜና አጻጻፍና አወቃቀርን ፣ የዜና አመራረጥ፣ አደራደርና አፈጻጸምን ፣ የአርትዖት ሥራን፣ የቋንቋ አጠቃቀምን ፣ የግብአት አሰባሰብና አጠቃቀምን አካቷል፡፡ የዜና ክፍሉ ከሌሎች የኮርፖሬሽኑ የተለያዩ የሥራ ክፍሎችና ከውጭ ተባባሪ አካላት ጋር የሚኖረውን ግንኙነት የሚመለከቱ ነጥቦችም ይዟል፡፡ በጋዜጠኞች ፣ በአርታኢያን፣ በዜና አስፈጻሚዎችና በሌሎች ጉዳዮ በሚመለከታቸው ባለሞያዎች አጠቃላይ የሥራ መመሪያ (guideline)ሆኖ ያገለግላል፡፡




## የዜና አሠራር ስታይል ቡክ

የዜና አሠራር ስታይል ቡክ የኢቢሲ የቋንቋ አጠቃቀም በተደራጀ መልኩ የአቀራረብ ደረጃውን የሚጠብቅበት ወጥ የሆነ የዜና አሠራር ስርዓት የሚያሰፍንበትን የዜና አሠራር መመሪያ ሆኖ የሚያገለግል ሰነድ ነው፡፡

ሰነዱ በዋናነት በአማርኛ ቋንቋ ላይ ያተኮረ ሲሆን ከፊደል አጠቃቀም ጀምሮ የቃላት ፣ ሐረጋት ዓረፍተ ነገሮችን ሐሳቦችን አደራጅቶ እንዴት መጠቀም እንደሚገባ በዝርዝር የያዘ ነው፡፡ የሕብረተሰቡ ወግና ባህል፣ የአኗኗር ዘይቤና ሕብረተሰባዊ ሕጐችን መሠረት ያደረገ የቋንቋው መሰረታዊ መዋቅር የሚከተል መመሪያ ነው፡፡



## የዜና ግራፊክስ አሰራር መመሪያ

የኢቢሲ ዜናና ፕሮግራሞች በአቀራረባቸው ፣ በአጠቃላይ ተቀይረው ለተመልካች ሳቢና ተፅዕኖ ፈጣሪ ለማድረግ አቅም የሚፈጥረው ዋነኛው መንገድ የግራፊክስ ዲዛይን አሰራር መተግበር ነው፡፡ በመሆኑም ኢቢሲ የራሱ የግራፊክስ ዲዛይን አሰራር መመሪያ በማዘጋጀት በአለም አቀፍ ሚዲያ ውድድር ውስጥ ተመራጭ ሚዲያ ለመሆን ጥረት ጀምሯል፡፡ ይህንን የግራፊክስ አሰራር መመሪያም በዜና ሥራ ውስጥ የግራፊክስ አጠቃቀም ምን መሆን እንዳለበትና የግራፊክስ አዘገጃጀት ሂደትና የባለሙያዎች ኃላፊነትን በግልፅ አስቀምጧል፡፡




<u>የኢቢሲ ማቋቋሚያ አዋጅና የሠራተኞች አስተዳደር ደንብ</u>

የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የሠራተኞቹን ጥቅምና መብት ለማስጠበቅ ግዴታቸውንና ኃላፊነታቸውን እንዲያውቁ ለማድረግና ስርዓት ባለው መንገድ ለመምራት የሠራተኞች ልዩ የአስተዳደር ደንብ አውጥቷል፡፡ ደንቡ ኮርፖሬሽኑ ከተቋቋመበት አዋጅ የሚመነጭ ሲሆን

በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 858/2006 አንቀጽ 7 እና በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የወጣ ነው፡፡




## <u>የዜጎች ቻርተር</u>

ኢቢሲ የተቋቋመበት ዓላማ ለማሳካትና በሀገሪቱ የህዳሴ ጉዞ የራሱን አሻራ ለማኖር በሚደረገው ጥረት ይበልጥ ውጤታማ የሚሆነው የአድማጭ ተመልካቾችን ቀጣይነትና ተከታታይነት ባለው መልኩ ማሳተፍ ሲቻል ነው፡፡ በግልፅነትና ተጠያቂነት መርህ በመመስረት ዜጎች የሥራችን ባለቤትና ዋንኛ ተባባሪ መሆናቸው ያምናል፡፡ በመሆኑም ይህ ሰነድ ዜጎች ከኢቢሲ ሊያገኙት የሚገባቸውን አገልግሎት በግልፅ የሚያስቀምጥና ተጠያቂነት ለማስፈን የሚረዳ አሰራርም የሚያጎለብት ሰነድ ነው፡፡

EBC

# የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን
# የዜጎች ቻርተር

Ethiopian Broadcasting Corporation
# Charter of Citizen